**የኮሎምቢያ ወረዳ የሰብዓዊ መብት ቢሮ**

**የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ፕሮግራም**

441 4th Street, N.W., Suite 570N

Washington, D.C 20001

Teléfono: (202) 727-4559; Fax: (202) 727-9589

**7.2007**

**የኮሎምቢያ ወረዳ የሰብዓዊ መብት ቢሮ**

**የቋንቋ ግልጋሎት ተሁለ ማግኛ ፕሮግራም መረጃ**

# የዲ.ሲ. የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ድንጋጌ ምንድን ነው?

በ2004 የተደነገገው የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ድንጋጌ በከንቲባ አንቶኒ ኤ.ዊሊያምስ በሚያዝያ 21/2004 ፀድቋል፤ ድንጋጌውም የወጣው ምንም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ወይም መጠነኛ ችሎታ (LEP/NEP) ላላቸው የኮሎምቢያ ወረዳ ነዋሪዎች በሕዝብ ግልጋሎቶች፤ ፕሮግራሞች፤ እና እንቅስቃሴ ዎች የበለጠ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።

ድንጋጌው የወረዳው መንግስት ፕሮግራሞችን፤ መሥሪያ ቤቶችን፤ ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ያላቸው ግልጋሎት ሰጪዎችን የሚከተለትን አራት ነገሮች እንዲፈጽሙ ያዛል።

- የአስተርጓሚ አስፈላጊነትን መመልከት እና የቃል ትርጉም ግልጋለት ማቅረብ።
- ጠቃሚ ለሆኑ ሰነዶች እንግሊዘኛ ወደአልሆነው ቋንቋ የጽሑፍ ትርጉም ግልጋሎት ማቅረብ፤ ምንም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ወይም መጠነኛ ችሎታ (LEP/NEP) ያላቸው የሕዝብ ብዛት 3% ወይም 500 ግለሰቦች ሆነው ሲገኙ፤ ከሁለቱ አንሶ የገኘው ይመረጣል፤ ግልጋሎት ከማያገኙት ወይም ግን ኙነት ከሚያደርጉት፤ ወይም ወደፊት ግልጋሎት ሊያገኙ ወይም ከተመቋሙ ግንኙነት ሊያገኙ ከሚችሉት አካላት መሃከል።
- የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ እቅድ ማውጣት እና ማስፈፀም።
- የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ አስተባባሪ መመደብ።

*ምንም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሉታ ወይም መጠነኛ ችሎታ ላላቸው የኮሎምቢያ ወ ረዳ ነዋሪዎች በሕዝብ ግልጋሎቶች፤ ፕሮግራሞች፤ እና እንቅስቃሴዎች የበለጠ ተሳትፎ እንዲኖራቸው።*

**ዲ.ሲ. ድንጋጌ 15-414**

የዲ.ሲ. የሰብዓዊ መብቶች ጽ/ቤት የሚከተለትን ስድስት ቋንቋዎች በወረዳው መንግስት በብዛት ግልጋሎት የሚሰጥባቸው ናቸው ብሎ ለይቷቸዋል፤ ስፓኒሽኛ፣ ቻይኒኛ፣ ቬትናሚኛ፣ ኮሪያንኛ፣ ፈረንሣይኛ እና አማርኛ።

ድንጋጌው አንቀጾቹ «ሥራ ላይ የሚውሉበትን ደረጃ» ጠብቀው እንዲፈፀሙ ያዛልን ይህም ማለት ከወረዳው የመንግስት ፕሮግራሞች፤ ከመሥሪያ ቤቶች፣ ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ያላቸው ግልጋሎት ሰጪዎች በድንጋጌው ውስጥ በዝርዝር ተጠቅሰዋል። በእያንዳንዱ ሒሳባዊ ዓመት ከሚያዝያ 21/2004 ጀምሮ አንቀጾቹን እንዲያከናውኑ።

የኮሎምቢያ ወረዳ የሰብዓዊ መብት ቢሮ (OHR) የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ድንጋጌን እንዲቆጣጠር በድንጋጌው ሥልየን ተሰጥቶታል፤ (OHR) የበላይ ማስተ ባበርን እና የቴክኒካል እርዳታችን ለመንግስት ፕሮግራሞች፤ ለመሥሪያ ቤቶች፣ ለከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ያላቸው ግልጋሎት ሰጪ ይሰጣልን፤ በተጨማሪም የቋንቋ ግልጋሎት ማግኘትን አስመልክቶ (OHR) የሕዝብ ብሶቶችን ለመከታተል፤ ለመመልከት እና ለመመርመር ሥልጣን አለው።

የኮሎምቢያ ወረዳ የሰብዓዊ መብት ቢሮ (OHR) ከከንቲባው የላቲኖ ጉዳይ ቢሮ (OLA)፣ ከከንቲባው የእስያውያን እና የፓስፊክ ደሴቶች ጉዳይ ቢሮ (OAPIA) በአፍሪካ ጉዳዮች የከንቲባው ጽ/ቤት (OAA)፤ እና የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ቅንኝት፣ ስደተኞችን ከሚደግፉ ሕብረተሰብ ውስጥ ካሉ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ካላቸው ጋር አብሮ ይሰራል።

## ድንጋጌው «ሥራ ላይ የሚውልበት ደረጃ»

ድንጋጌው ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በተግባር የሚያውሉ፤

- የጤና መስሪያ ቤት
- የሕዝብ ግልጋሎት መስሪያ
- የሠራተኛ ግልጋሎት መስሪያ ቤት
- የከተማ ፖሊስ መስሪያ ቤት
- የኮሎምቢያ ወረዳ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
- የእቅድ ጽሑፈት ቤት
- የእሳት እና የአስቸኳይ የጤና ግልጋሎት መስሪያ ቤት
- የሰብዓዊ መብት ቢሮ

ድንጋጌውን ከጥቅምት 1/2004 ጀምሮ በተግባር የሚያውሉ፣

- የቤት እና የሕብረተሰብ ልማት መስሪያ ቤት
- የአእምሮ ጤና መስሪያ ቤት
- የተሽከርካሪ መኪኖች መስሪያ ቤት
- የልጆች እና የቤተሰቦች ግልጋሎት ድርጅት
- የአልኮል መጠጦች መቆጣጠሪያ አስተዳደር
- የተጠቃሚዎች እና የመቆጣጠሪያ ጉዳይ መስሪያ ቤት

ድንጋጌውን ከጥቅምት 1/2005 ጀምሮ በተግባር የሚያውሉ፣

- የመናፈሻ እና የመዝናኛ መስሪያ ቤት
- የአዛውንቶች ቢሮ
- የኮሎምቢያ ወረዳ የሕዝብ መጻሕፍት ቤት
- የሠራተኛ ጉዳይ ቢሮ
- የመዋዋያ እና የምልመላ ቢሮ
- የማረሚያ መስሪያ ቤት
- የሕዝብ ግልጋሎት መስሪያ ቤት
- የቀረጥ እና የገቢ ቢሮ

ድንጋጌው በጥቅምት 1/2006 ጀምሮ የቀሩት ሌሎች ክፍሎችን ያካትታል፣

- ዲ.ሲ. የቤቶች ባለሥልጣን
- የሕዝብ መማክርት ጽ/ቤት
- የአገር ውስጥ ደህንነትና የድንገተኛ ጊዜ አስተዳደር ኤጀንሲ
- እንዲሁም ሽፋን ላላቸው አካላት በሙሉ